# ኮሮናቫይረስን(COVID-19) በማስመልከት አስፈላጊ ማሳሰቢያ በከተማ እና አካባቢዎች ለምትኖሩ ለመላው ስደተኞች እና ጥገኝነት-ፈላጊዎች በሙሉ በስደተኞች ጉዳዮች እና ጽሕፈት በት የቀረበው፣ የኬኒያ መንግስት

**(የተለቀቀበት፥ 10 ሐምሌ 2020)**

የኬኒያ መንግስት COVID-19 የበለጠ እንዳይስፋፋ ለመከላከል ገደቦችን ኣውጥቷል። እነዚህ ገደቦች ሰኣት እላፊ ከምሽቱ 9 አስከ ማለዳ 4 ሰኣት ድረስ፣ በኣንድ ኣካባቢ ከ15 ሰዎች በላይ መሰብሰብ የሚከለክል እንዲሁም በህዝብ ቦታዎች ላይ የፊት ጭንብል ማድረግ ናቸው።

የCOVID 19 ስርጭትን ለመቀነስ መንግስት ባወጣው መመሪያ ምክንያት ስደተኞቹን ለመቀበል፣ **በቢሮው ዉስጥ ምንም የፕሮተክሽን ሰራተኞች በኣካል የሉም**። ተጨማሪ ማስታወቂያ አስከሚወጣ ድረስ፣ የፕሮተክሽን ጉዳዮች ማንሳት የሚፈልጉ ስደተኞች በዝህ ማድረግ ይችላሉ፥

- ***የUNHCR የእገዛ መስመር በመደወል፥ 0800720063 (ነጻ)*** *ወይም*
- *በእመይል* helpline.kenya@unhcr.org *ላይ።*

የእገዛ መስመሩ ለክትትል ጥያቀዎቹን ለUNHCR ፕሮተክሽን ሰራተኞች ያስተላልፋል።

እንደ ስደተኛነትዎ ሁል ጊዜ የመንግስት ህጎችን እና ደንቦችን መተባበር እና መከተል ይጠበቅብዎታል። ከ UNHCR ቢሮ ዉጭ መጠለያ ወይም መሰብሰብ የመንግስት ገደቦችን የሚጥስ ነው፣ እና እራስዎን፣ ልጆችዎን እና ለሎች ሰዎችን ለCOVID-19 የመጋለጥ ወይም የመሰራጨት ኣደጋ ላይ ነዎት። **ከUNHCR ቢሮ ዉጭ ወይም ለላ ቦታ መጠለያ ወይም መሰብሰብ ለመቀጠል ከወሰኑ፣ በሕግ ኣስፈላጊዉን እርሚጃ እንደሚወስድ መንግስት ኣሳስቧል።**

- ➢ እባክዎን የገንዘብ እርዳታ የተቀበሉ ወይም የገንዘብ እርዳታን የሚቀበሉ ሰዎች **ተጨማሪ እርዳታ እንደማይሰጣቸው** ይመከሩ።
- ➢ **የሶስተኛ ኣገር ወይም ሪሰትልመንት ሂደት በመቆም ላይ ነው** እናም በነዚህ ጊዘያት ለሶስተኛ ኣገር ኣድስ ሰዎች ኣይለይም።
- ➢ የፕሮተክሽን ጉዳይን ሪፖርት ማድረግ ከፈለጉ፣ እባክዎን ወደ የእገዛ መስመር አደዉሉ። **ከUNHCR ቢሮ ዉጭ በሚሆኑበት ጊዘ ከማንኛዉም የUNHCR ሰራተኛ ኣያገኙዎትም።**
- ➢ **በከተሞች የሚደረግ ድጋፍ እጅግ በጣም ውስን ነው።** በናይሮቢ ወይም በለሎች የከተማ ኣካባቢዎች በእራስዎ ማስተዳደር ካልቻሉ እና እርዳታ ከፈለጉ ምግብ፣ ዉሃ፣ ትምህርት፣ ጠና እና መጠለያ ጨምሮ አገልግሎቶች ወደሚገኙበት ወደ ካኩማ ከመዛወር ለላ ኣማራጭ የለም።
- ➢ **ወደ ካኩማ ለመሄድ ከፈለጉ**፣ እባክዎን የእገዛ መስመር ይደውሉ እና እርስዎ ወደ ካምፕ መቸ እንደሚሄዱ መረጃ ይሰጥዎታል።

እባክዎን ያስታውሱ ስብሰባዎች በCOVID-19 ግዜ አይፈቀድም። በአንድ ስብሰባ ላይ በመሳተፍ፣ እራስዎን እና ለሎችን ለCOVID-19 ያጋልጣሉ። ***መንግስት COVID-19 እንዳይሰራጭ ለመከላከል ማንኛውንም ማሰባሰብ ለማስቆም አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት።***

እነዚህ ግዘያት ለማኒም ቀላል ኣይደሉም። እርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎን የሚከተሉትን የኣደጋ ጊዘ እርዳታ ቁጥሮች ይመልከቱ፥

| | |
|---|---|
| *ለምዝገባ/ሰነድ ድንገተኛ ኣደጋዎች፥* የስደተኛ ጉዳዮች ጽ/በት ሻውሪ ሞዮ፥ 0772057770 | *ጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት መስመር፥* 1195/ 0800720501 |
| *ለጠና ድንገተኛ ኣደጋዎች፥* NCCK 0704873342 / 0723281352/ 0723281362 | *ለNHIF-የተያያዙ ጉዳዮች(ብሐራዊ ሆስፒታል እንሹራንስ ፈንድ)፥* 0740049502 |
| *ለህጋዊ ድንገተኛ ኣደጋዎች(መያዝ፣ ከፖሊስ ጋር ችግሮች)፥* Kituo cha Sheria 0720806531 | *የህጻናት ጥበቃ መስመር፥* 116 |
| *የምክር መስመር፥* 1190/ 1199/ 0721 336017 | |

COVID 19 በበሽታው ከተያዘው ሰው በቀጥታ ጠብታዎች(ሳል/በማስነጠስ)፡ በተዘዋዋሪ በበሽታው በተያዘው ሰው ከሚጠቀምባቸው ገጽታዎች ወይም እቃዎች ጋር ኒክኪ በማድረግ ይተላለፋል። እንደ ትኩሳት፣ ሳል፣ የትንፋሽ እጥረት እና የመተንፈስ ችግሮች ያሉ **ማንኛውም የ COVID-19 ምልክቶች** ካለብዎ **እባክዎን የጠና ጥበቃ ሚኒስተርን** በ 0800721316(ነጻ)፡ 0732353535፡ ወይም 0748592558 ለመመሪያ **ያነጋግሩ።**







**0800720063**